# ረቂቅ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ላይ አንዳንድ አስተያየቶች

አምነስቲ ኢንተርናሽናልበበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ረቂቅ አዋጅ ላይ  አስተያየቶቹን ትሲያቀርብ በታላቅ ደስታነው፡፡[1]  ረቂቅ አዋጁ አሁን በስራ ላይ ካለው አዋጅ ጋር ሲነፃፀር መሰረታዊ መሻሻሎችን ያካተተ ሲሆን፣ በነፃነት የመደራጀትና ሀሳብን የመግለፅ መብቶችን በላቀ መልኩ የሚያከብር ነው፡፡ ነገር ግን በረቂቅ አዋጁ ውስጥ የተካተቱ አንዳንድ አንቀጾች ዜጎች እነዚህን መብቶች እንዳይጠቀሙ የሚገድቡ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት አፋኝ የሆኑ ህጎችን ከአለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች መስፈርቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ ለማሻሻል በገባው ቃልና ባሳየው ቁርጠኝነት መሰረት አምነስቲ ኢንተርናሽናል ረቂቅ አዋጁን የበለጠ ለማጠናከር የሚረዱ ምክረ ሃሳቦችን እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡ ይህም ለሲቪል ማህበራት እና ለሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች ምቹ የሆነ ሁኔታን በመፍጠር የኢትዮጵያ መንግስት የጀመረውን የለውጥ ጉዞ እንዲያግዙ ያስችላቸዋል፡፡[2]

## ረቂቅ አዋጁ የተዘጋጀበት አውድ

የኢትዮጵያ መንግስት የጀመረው የለውጥ እንቅስቃሴ አንዱ ኣካል አፋኝ የሆኑ ህጎችን ማሻሻልና የተቋማትን ነፃነት፣ ገለልተኛነትና አቅም ማጠናከር ሲሆን ይህንንም ለማሳካት በቅድሚያ መሻሻል ያለባቸው ተብለው የተለዩት ህጎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/09፣ ፀረ ሽብር አዋጅ ቁጥር 652/09 እና የመገናኛ ብዙኅን እና የመረጃ ነፃነት ኣዋጅ ቁጥር 509/2008 ናቸው፡፡ እነዚን ህጎች ለማሻሻል የጠቅላይ አቃቤ ህግ ጽ/ቤት እ.ኢ..አ. ሰኔ 29 2018 ዓ.ም ታዋቂ የህግ ባለሙያዎችን ያካተተ የህግ አማካሪ ምክር ቤት ያቋቋመ ሲሆን ምክር ቤቱ የማሻሻያ ረቂቅ ወይም አዲስ አዋጆችን ማዘጋጀትን ጨምሮ የህግ ማሻሻል ስራውን በዋናነት የመምራት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በምክር ቤቱ ስር ያሉ ንኡስ የስራ ቡድኖች እየሰሩ ያሉትን የህግ ማሻሻያ ስራዎች  በቅርበት ሲከታተል ቆይቷል፡፡ የምክር ቤቱ እና በስሩ ያሉ የስራ ቡድኖች አባላት የተጣለቸውን ሀላፊነት ለመወጣት ያሳዩትን ቁርጠኝነት እንዲሁም ህጎቹን ከህዝብና ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመምከር በፍጥነት ለመገምገም የሰሩትን ስራ ሳያደንቅ አያልፍም፡፡

## የረቂቅ አዋጁ ትንተና

እንደ አምነስቲ ኢንተርናሽናል ግምገማ ለጠቅላይ አቃቤ ህግ ጽ/ቤት የገባውን ረቂቅ አዋጅ አሁን በስራ ላይ ካለው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/09 ጋር ሲነፃፃር ጉልህ አወንታዊ ማሻሻያዎችን ያካተተ ነው፡፡[3]ረቂቅ አዋጁ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/09 በነፃነት የመደራጀትና ሃሳብን የመግለፅ መብቶች ላይ የጣላቸውን ግደባዎች በማንሳት ጥሩ እመርታ አሳይቷል፡፡ ረቂቀ አዋጁ ውስጥ ከተጠቃለሉ ዋና ዋና ለውጦች መካከል አንዱ የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የመልካም አስተዳደር፣ ፀረ-ሙስና፣ የግጭት አፈታት  እና ተመሳሳይ ጉዳዩች ላይ የሚሰሩ ሲቪል ማህበራት ላይ የተጣለው የገቢ ምንጭ ገደብ መነሳቱ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/09 ያቋቋመው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ በአዋጁ የተሰጡትን ሰፊ ጣልቃ-ገብነትን የሚፈቅዱ እና የሲቪል ማህበራትን ነጻነት የሚፃረሩ ስልጣኖችን ሰርዟል፡፡ ረቂቅ አዋጁ የግለሰቦች የሲቪል ማህበራት አባል የመሆን መብት ላይ ዜግነትና ነዋሪነት ላይ ተመሰርቶ ተጥለው የነበሩ ገደቦችን አንስቷል፡ ፡ ይህም ሲቪል ማህበራት ስራቸውን ለማስኬድ የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ምንጭ ለማስፋት አዎንታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ማሻሻያዎች  አንፃር እኩል ጠቃሚነት ያለው ሌላው በረቂቅ አዋጁ የተጠቃለለው ማሻሻያ የውጪ ሲቪል ማህበራትን ጨምሮ ሁሉም ሲቪል ማህበራት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ምዝገባን በተመለከተ የሚያስተላልፉቸውን ውሳኔዎች የመቃወምና ጉዳዩ በፍርድ ቤት ጭምር እንዲታይ የማድረግ መብት ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት አስፈላጊና ጠቃሚ ማሻሻያዎች እንዳሉ ሆነው አምነስቲ ኢንተርናሽናል ባደረገው ግምገማ በረቂቅ አዋጁ ውስጥ የተጠቃለሉ አንዳንድ አንቀጾች በነፃነት የመደራጀትና ሃሳብን የመግለፅ መብቶች ላይ አግባብነት የሌላቸው ገደቦችን የሚጥሉ ሆነው

---

[1] አምነስቲ ኢንተርናቲናል በእጁ ላይ ያለው ረቂቅ አዋጅ በህግ አማካሪ ምክር ቤቱ በቀን 21 ጥቅምት 2018 ዓ.ም. እ.ኢ.አ. ለጠቅላይ አቃቤ ጽ/ቤት የተላለፈው ነው፡፡ በዚህ ዶክመንት ውስጥ የተጠቀሱት የረቂቅ አንቀጾች ኦፊሴላው ያልሆኑ አምንስቲ ኢንተርናሽናል ከአማርኛ ወደ እንግሊዝኛ የተረጎማቸው ናቸው፡፡ ረቂቅ አዋጁ በጠቅላይ አቃቤ ጽ/ቤት ተመርምሮ ተጨማሪ ማስተካከያዎች ተደርጎበታል፡፡ ይህ የረቂቁ አዋጅ ትንታኔ አምነስቲ ኢንተርናቲናል በረቂቅ አዋጁ በጠቅላይ አቃቤ ጽ/ቤት በኩል እ.ኢ.አ. በህዳር ወር 2018 ዓ.ም.  የተደረጉ ዋና ዋና ማስተካከያዎች በተመለከተ በሰበሰበው መረጃ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡አምነስቲ ኢንተርናቲናል ረቂቅ አዋጁ የደረሰበትን ደረጃ በእርግጠኝነት መናገር ባይችልም የጠቅላይ አቃቤ ጽ/ቤት እ.ኢ.አ. 12 ህዳር 2018 ዓ.ም. እንዳስታውቀው አዋጁ በቅርቡ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ለውይይት ከቀረበ በኃላ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመጨረሻ ተውያይቶበት ያፀድቀዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

[2] አምነስቲ ኢንተርናቲናል ከኢትዮጵያ የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ እና ምክትል ጠቅላይ አቃቤ ጋር እ.ኢ.አ. በ21 ህዳር 2011 ዓ.ም. ተገናኝቶ የተወያየ ሲሆን በዚህ ዶክመንት ላይ በተነሱና በፊት በነበሩት ረቂቅ አዋጅ ይዘት ላይ ያለውን ሃሳብ አቅርቦ ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡ ይህን ረቂቅ አዋጁ ላይ ያደረገውን ትንተና እና ምክረ ሃሳቦችን ያሚጠቃልለውን ዶክመንትንም ለጠቅላይ ሚኒስትር ት/ቤጽ እና ለጠቅላይ አቃቤ ህግ ት/ቤጽ በኢ-ሜይል እ.ኢ.አ. በቀን 20 ታህሳስ 2018 ዓ.ም. ልኳል፡፡

[3] አምነስቲ ኢንተርናቲናል፣ *የሰብዓዊ መብት ስራን ማደናቀፍ፡ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ህግ ያስከተለው ውጤት፣* እ.ኢ.አ.  12 የካቲት 2012 የታተመ (AFR25/002/2012)

ተገኝተዋል፡፡ ኢትዮጵያ የአፍሪካ የሰብዓዊና የህዝቦች መብቶች ቻርተርን እና የተባበሩት መንግስታትን አለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አፅድቃለች፡፡ በነፃነት የመደራጀት መብት በነኚህ ሁለት የሰብዓዊ መብት ሰነዶች ተረጋግጦ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ የተባበሩት መንግስታት እና አህጉራዊ የሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር የተቋቋሙ አካላት እንዲሁም ገለልተኛ የሆኑ የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች በነፃነት የመደራጀት መብትን በተመለከተ በርካታ ጠቃሚ የሆኑ መመሪያዎችንና ገዢ የሆኑ ትርጉዋሜዎችን አሰናድተዋል፡፡ ከነዚህም መካከል እ.ኤ.አ. 2017 በአፍሪካ የሰብዓዊና የህዝቦች መብቶች ኮሚሽን የፀደቀው በአፍሪካ በነፃነት የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ መብት በአፍሪካ መመሪያ ተጠቃሽ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በነፃነት የመደራጀት መብት ላይ የሚጣል ማንኛውም ዓይነት ገደብ በጠበበ መልኩ መዘጋጀት ያለበት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ብሄራዊ ወይም የሕዝብ ደህንነትን፣ ሰላምና ፀጥታን፣ የህዝብ ጤና ወይም የሞራል ሁኔታን እና የሌሎችን መብቶችና ነፃነቶች ለመጠበቅ አስፈላጊ[4] የሆነ መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪ አዚህ መብት ላይ የሚጣሉ ሁሉም ገደቦች አግባብ ያላቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥ ጥብቅ የሆኑ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው፡፡ አምነስቲ ኢንተርናሽናል ባደረገው ትንተና እነዚህን መስፈርቶች የማያሟሉ በረቂቅ አዋጁ ውስጥ የተጠቃለሉ አንቀጾችን ከዚህ በታች በተቀመጠው መልኩ ነቅሶ አውጥቷል፡፡

*ሀ. የምዝገባ መስፈርቶች*

*የረቂቅ አዋጅ አንቀፅ 60፡ የበጎ አድረጎት ድርጅትና ማህበራት ምዝገባ*

1. *ማንኛውም/ሁሉም ማህበራት/ድርጅቶች በዚህ ህግ መሰረት በኤጀንሲው መመዝገብ አለባቸው፡፡*

በዚህ አንቀፅ መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት፣ በበጎ አድረጎት ድርጅቶችና ማህበራት ቦርድ በሚቋቋመው የበጎ አድረጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የመመዝገብ ግዴታ አለባቸው፡፡ በስራ ላይ ባለው ህግ መሰረት ተመዝግበው እየሰሩ የሚገኙ የበጎ አድረጎት ድርጅቶችና ማህበራት በአዲሱ ህግ መሰረት ድጋሚ መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡[5] ይህ አንቀጽ አላስፈላጊ የሆነ የፍቃድ ስርዓትን የሚዘረጋ ሲሆን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ወደ ስራ ለመግባት አግባብ ላለው የመንግስት አካል ከማሳወቅ ባለፈ የመመዝገብ ግዴታ ይጥልባቸዋል፡፡ ይህ የረቂቅ አዋጁ ድንጋጌ ከላይ የተጠቀሰውን በአፍሪካ የሰብዓዊና የህዝቦች መብቶች ኮሚሽን የፀደቀው በአፍሪካ በነፃነት የመደራጀትና ማህበራትን ማቋቋም ላይ የወጣው መመሪያ ጨምሮ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኙ፣ በነፃነት የመደራጀት መብት መስፈርቶችን የሚፃረር ነው፡፡ ለምሳሌ የአፍሪካ የሰብዓዊና የህዝቦች መብቶች ኮሚሽን ያፀደቀው መመሪያ በግልፅ እንዳስቀመጠው የሲቪል ማህበራት ምዝገባን በተመለከተ የሚዘረጋ ማንኛውም ስርዓት አግባብ ላለው የመንግስት አካል ማሳወቅ ላይ የተመሰረተ ስርዓት (notification regime) መሆን አለበት፡፡ መመሪያው ሲቨል ማህበራት ወደ ስራ ለመግባት ቅድመ ፍቃድ የማግኘት ግዴታን የሚጥሉ የምዝገባ ስርዓቶች አግባብነት የሌላቸው መሆኑን ያስቀምጣል፡፡ ሲቪል ማህበራቶች ቅድመ ፍቃድ የማግኘት ግዴታ ሳይጣልባቸው ህጋዊሰውነታቸው አግቢብ ላለው የመንግስት አካል ካሳወቁበት ቀን ጀምሮ በህጋዊ ግምት (legal presumption) መቋቋም እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡[6]

ሲቪል ማህበራትን የመመዝገብ ዋነኛው ዓላማ ግለሰቦችና ህብረተሰቡ ከማህበራቱ ጋር በሚያደርጉት የውልና ከውል ውጪ በሆኑ ግንኙነቶች መብቶቻቸውንናና ፍላጎቶቻቸውን ለመጠበቅ ሲሆን ይህን ህጋዊ የሆነ ዓላማ በ"ማሳወቅ ስርዓት" ማሳካት የሚችል ሲሆን ይህ ስርዓት ግለሰቦች በነፃነት የመደራጀት መብታቸውን ሙሉ በሙሉ እንዲጠቀሙ የሚያስችል ጭምር ነው፡፡ የተባበሩት መንግስታት የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ ነፃነት ልዩ ራፖርተርም የተለያዮ ሀገራትን ልምድ በመጥቀስ ለ"ማሳወቅ ስርዓት" ድጋፍን እንደሚከተለው ሰጥቷል፡-

> "ማህበራት ያቋቋሟቸው ሰዎች ስለመቋቋማቸው አግባብነት ላለው የመንግስት አካል ባሳወቁበት ቅፅበት ህጋዊ ሰውነት ይኖራቸዋል፡፡ በአብዛኛዎቹ ሀገራት የማሳወቁ ሂደት የሚከናወነው በፅሁፍ ሲሆን መካተት ያለባቸው ጉዳዮች አስቀድመው በህግ የተቀመጡ ናቸው፡፡ በፅሁፍ የማሳውቅ ግዴታው ግን ማህበራትን ለመፍጠር አስገዳጅ የሆነ ቅድመ ሁኔታ ሳይሆን መንግስት ማህበራቱ መቋቋማቸውን ለመመዝገብ የሚያስችለው ስርዓት ነው፡፡ እንደዚህ

---

[4] የአለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን፣ 1966 ፀደቀ፣ ተ.መ.ድ. G.A. Res. 2200A (XXI), 21 U.N. GAOR Supp. (No.16) at 59, U.N. Doc.A/6316 (1966) , 999 U.N.T.S. 302, እ.ኢ.አ. በ23 የካቲት 1976 በስራ ለይ ዋለ፡፡ ኢትዮጵያ እ.ኢ.አ. በ1993 ዓ.ም. አፀደቀችው፡፡ አንቀጽ 21

[5] አንቀጽ 2(1) ላይ በተቀመጠው ትርጓሜና በአንቀጽ 88(2) መሰረት አሁን በስራ ላይ ባለው አዋጅ መሰረት የተመዘገቡ በጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ጨምሮ ሁሉም በጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በድጋሚ የመመዝገብ ግዴታ አለባቸው፡፡

[6] የአፍሪካ የሰብዓዊና የህዝቦች መብቶች ኮሚሽን፣ *በአፍሪካ በነፃነት የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ መብት በአፍሪካ መመሪያ፣ 60ኛ መደበኛ ጉባዔ፣ ኒያሚ-ኒዤር፣ እ.ኢ.አ. 8-22 ግንቦት 2017፣ አንቀጽ* 13 http://www.achpr.org/files/instruments/freedom-associationassembly/guidelines_on_freedom_of_association_and_assembly_in_ africa_eng.pdf (በመጨረሻ የታየው እ.ኢ.አ. 30 ጥቅምት 2018)

> አይነት የ"ማሳወቅ ስርዓት" በብዙ ሀገሮች ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል (ለምሳሌ ኮት ዲቯር፣ጂቡቲ፣ ሞሮኮ፣ ፖርቹጋል፣ ሴኔጋል፣ ሰዊትዘርላንድ እና ኡራጓይ)፡፡"[7]

ከዚህም በተጨማሪ ራፖርተሩ የውጪ ሲቪል ማህበራት ቅርንጫፎችን በሚከፍቱበት ግዜ እንዲሁም የሙያ ማህበራትና የሲቪል ማህበራት ጥምረቶች በሀገር አቀፍም ይሁን በአለም አቀፍ ደረጃ በሚቋቋሙበትጊዜ ይህንን ስርዓት መከተል ተገቢ እንደሆነ ምክረ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡[8]

ከዚህ በተጨማሪ ረቂቅ ህጉ የምዝገባ ስርዓቱን በሚጥሱ ማህበራት ላይ ቅጣቶችን ባይጥልም፤ እነዚህ ማህበራት ሊቀጡ የሚቻሉበት ዕድል እንዳለ ረቂቅ አዋጁን ከወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 791 ጋር አጣምሮ በማንበብ መረዳት ይቻላል፡፡

> ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 791፡ ማንም ሰው በዚህ የወንጀል ሕግ ወይም ለተለዩ የሙያ ወይም የንግድ ሥራዎች በተደነገጉ ሕጎች መሰረት ከሚያስቀጣው ሁኔታ ውጭ የኢንዱስትሪ እና የንግድ ድርጅቶችን፣ እደጥበባትን፣ ባለሙያዎችን፣ ጊዜያዊ ወይም ወቅታዊ ሥራዎችን ወይም የሙያ ማሕበራትን እና ማናቸውም ዓይነት ማህበሮችን ስለመፍቀድ ወይም ስለመቆጣጠር የወጣውን ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ የተላለፈ እንደሆነ፡ በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቦታ እስራት ይቀጣል፡፡[9]

ይህ ከወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የተወሠደ አንቀጽ መንግስትን ይነቅፋሉ ተብለው በሚታመኑ እና ባልተመዘገቡ ማህበራት ውስጥ አባል የሆኑ ግለሰቦች እና ካልተመዘገቡ ማህበራት ጋር የሚሰሩ ሌሎች ማህበራት ላይ በዘፈቀደ እርምጃ እንዲወሰድ መንገድ የሚከፍት ነው፡፡ ያልተመዘገቡ ማህበራት ላይ የተጣሉ የወንጀል ቅጣቶችን ግብታዊ ተፈጻሚነት የተገነዘበው የተባበሩት መንግስታት የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ ነፃነት ልዩ ራፖርተር ባልተመዘገቡ ማህበራት ውስጥ አባል የሆኑ ግለሰቦች በወንጀል እንጠየቃለን የሚል ስጋት ሣያድርባቸው ህጋዊ የሆኑ ማናቸውንም እንቅስቃሴዎችን ከሌሎች ጋር በመተባበር እንዲሁም ሰላማዊ በሆነ መልኩ በመሰብበሰብ መስራት እንደሚችሉ አጽንኦት ሰጥቶ አሳስቧል፡፡[10]

**ምክረ ሃሳብ፤**

**ሀ. አንቀፅ 60(1) ተሸሽሎ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን መቋቋማቸውን ማሳወቅ ብቻ በጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን ለማቋቋም፣ ህጋዊ ሰውነት ለመስጠትና ስራ እንዲጀምሩ በቂ መስፈርት እንዲሆን ማድረግ**

ለ. ለምዝገባ የተቀመጡ ጊዜ ገደቦች

*የረቂቅ አዋጅ አንቀፅ 60፡ የበጎ አድረጎት ድርጅቶችና ማህበራት ምዝገባ*

2. *በአዋጁ የተደነገጉ ቅደመ ሁኔታዎች መሟላታቸው እንደተረጋገጠ ኤጀንሲው ምዝገባውን አከናውኖ ለሀገር ውስጥ የበጎ አድረጎት ድርጅቶችና ማህበራት ማመልከቻካስገባበት ቀን አንስቶ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ፤ ለውጪ ሀገር የበጎ አድረጎት ድርጅቶችና ማህበራት ደግሞ ማመልከቻ ከገባበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ ባሉት 45 ቀናት ውስጥ የምዝገባ ሰርትፊኬት መስጠት ይኖርበታል፡፡*
3. *ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ በተቀመጡት የጊዜ ገደቦች መሰረት ኤጀንሲው የምዝገባ ሰርትፊኬቱን ካልሰጠ ወይም የምዝገባ ማመልከቻው ውድቅ መሆኑን ካላሳወቀ፣ ኤጀንሲው ማመልከቻውን ውድቅ ለማድረግ ምንም አይነት ምክንያት እንደሌለው የህግ ግምት ይወሰዳል፡፡*
4. *ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ በተቀመጡት የጊዜ ገደቦች መሰረት ከኤጀንሲው የምዝገባ ሰርትፊኬት ያልተሰጠው አመልካች ጉዳዩን ለኤጀንሲው ቦርድ በ30 ቀናት ውስጥ በይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡*

---

[7] ተ.መ.ድ፣ *የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ ነፃነት ልዩ ራፖርተር ሪፓርት፣ ማይና ኪያይ፣* የሰብዓዊ መብት ምክር ቤት 20ኛ ስብስባ A/HRC/20/27, እ.ኢ.አ. 21 ግንቦት 2012, አንቀጽ 58፣ https://www.ohchr.org/Documents/HRBodies/HRCouncil/RegularSession/Session20/A-HRC-20-27_en.pdf (በመጨረሻ የታየው እ.ኢ.አ. 30 ጥቅምት 2018)

[8] ተ.መ.ድ፣ *የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ ነፃነት ልዩ ራፖርተር ሪፓርት፣ ማይኒያ ኪያይ፣* የሰብዓዊ መብት ምክር ቤት 20ኛ ስብስባ A/HRC/20/27, እ.ኢ.አ. 21 ግንቦት 2012, አንቀጽ 59፣ https://www.ohchr.org/Documents/HRBodies/HRCouncil/RegularSession/Session20/A-HRC-20-27_en.pdf (በመጨረሻ የታየው እ.ኢ.አ. 30 ጥቅምት 2018)

[9] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክሪያሳዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አዋጅ ቁጥር 414/2008፣ አንቀጽ 791

[10] ተ.መ.ድ፣ *የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ ነፃነት ልዩ ራፖርተር ሪፓርት፣ ማይኒያ ኪያይ፣* የሰብዓዊ መብት ምክር ቤት 20ኛ ስብስባ A/HRC/20/27, እ.ኢ.አ. 21 ግንቦት 2012, አንቀጽ 56፣ https://www.ohchr.org/Documents/HRBodies/HRCouncil/RegularSession/Session20/A-HRC-20-27_en.pdf (በመጨረሻ የታየው እ.ኢ.አ. 30 ጥቅምት 2018)

5. *ቦርዱ በይግባኝ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ውሳኔውን በ60 ቀናት ውስጥ ማስተላለፍ አለበት፡፡*
6. *ቦርዱ ለበጎ አድረጎት ድርጅቱ ወይምማህበሩ የምዝገባ ሰርተፊኬት ላለመስጠት በቂ ምክንያት የለም ብሎ ከወሰነ፣ የምዝገባ ሰርተፊኬት በአስቸኳይ እንዲሰጥ ማዘዝ ይኖርበታል፡፡*

ረቂቅ አዋጁ ለምዝገባ የጊዜ ገደቦችን እንደሚያስቀምጥ አምነስቲ ኢንተርናሽናል አስተውሏል፡፡ ነገር ግን በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 51(2)እና 51(5) ላይ የሰፈሩት የጊዜ ገደቦች በተለይ ለውጪ ድርጅቶችና ማህበራት ከመጠን በላይ የተራዘሙ ናቸው፡፡ ለይግባኝ የተቀመጡትን የጊዜ ገደቦች ጋር ደምረን ካየነው አጠቃላይ የምዝገባ ጊዜው ለሀገር ውስጥ በጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት 4 ወር፣ ለውጪዎቹ ደግሞ ከ4 ወር በላይ የሚፈጅ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በአንቀፅ 63 መሰረት በጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ህጋዊ ሰውነት ለማግኘት ምዝገባቅድመ ሁኔታ ከመሆኑ አንፃር እጅግ የተራዘመ የምዝገባ ጊዜ የመደራጀት መብትን ይገድባል፡፡

ከዚህ የተሻለውና የመደራጀት መብትን የተሻለ የሚያከብረው የህግ ማዕቀፍ የማህበራት ምስረታ የሚጀምረው ማመልከቻ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡[11] የአፍሪካ ሰብዓዊና የህዝቦች መብቶች ኮሚሽን ያፀደቀው በነፃነት የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ መብት በአፍሪካ መመሪያ እንዳስቀመጠው "የምዝገባ ስነ ስርዓቶች ቀላል፣ ግልፅ፣ ከመድሎ የፀዱ እና ለመተግበር የማያስቸግሩ መሁን ያለባቸው ሲሆን ግምታዊ የሆኑ መስፈርቶችን ማካተት የለባቸውም፡፡"[12] መመሪያው ማህበራት ተመሰረቱ የሚባለው ማመልከቻ ካስገቡበት ቀን ጀምሮ መሆኑን እንደሚከተለው ያትታል፡-

> "ማህበራት የምስረታ ማሳወቂያ ማመልከቻ ማስገባታቸውን የሚመሰክር ኦፊሻላዊ ዶክመንት ማመልከቻውን ሲያስገቡ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ አግባብ ያለው የመንግስት አካል ይህንን ዶክመንት ካልሰጠ ማመልከቻው መግባቱን የሚያረጋግጡ ሰነዶች ለምሳሌ የፖስታ ሰነዶች ወይም ገቢ የተደረገው ማመልከቻ ቀሪ ኮፒ ማመልከቻው እንደገባ በቂ ማረጋገጫ ተደርገው መወሰድ አለባቸው፡፡"[13]

በተመሳሳይ መልኩ የተባበሩት መንግስታት የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ ነፃነት ልዩ ራፖርተርም በሰጡት ምክረ ሀሳብ "በቅድመ ማሳወቅም ሆነ በቅድመ ፍቃድ ስርዓት የመመዝገብ ሀላፊነት ያለባቸው የመንግስት አካላት በፍጥነት ምላሽ እንዲሰጡ በህግ መገደድ ያለባቸው ሲሆን ህጉ በተጨማሪ ለማመልከቻና ቅሬታዎች መልስ መስጫ አጭር የጊዜ ገደቦችን ማስቀመጥ ይጠበቅበታል፡፡"

**ምክረ ሃሳብ፤**

**ሀ. በአንቀፅ 60 ንዑስ አንቀጽ 2-5 የተዘረዘሩት ለምዝገባ ማመልከቻና የኤጀንሲውን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ የተባሉ ጉዳዮችን ውሳኔ ለማስተላለፍ የተቀመጡ የጊዜ ገደቦችን ማሳጠር፤ እና**

**ለ. በአንቀፅ 60 ስር ኤጀንሲው የምዝገባ ማመልከቻ መቀበሉን የሚያረጋግጥ ምስክርነት ወይም ማረጋገጫ ሰነድ እንዲሰጥ የሚያስገድድ ንዑስ አንቀጽ ማስገባት**

ሐ. የውጪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የሚቋቋሙበት አላማና እንቅስቃሴዎቻቸው ላይ የተጣሉ ገደባዎች

*የረቂቅ አዋጅ አንቀፅ 64፡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የሥራ ነፃነት*

5. *በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም፤ የውጪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የፖለቲካ ፓርቲዎች ውሳኔ ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር የአድቮካሲ ወይም የማሳመን ስራ ላይ መሰማራት አይችሉም፡፡ በተጨማሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አግባብ ካለው የመንግስት አካል ልዩ ፍቃድ ከልተሰጣቸው በቀር መራጮችን ማስተማርና ምርጫ መታዘብ አይችሉም፡፡*

---

[11] ከላይ በክፍል "ለ" ስር ያለውን ትንትኔ ይመልከቱ

[12] የአፍሪካ የሰብዓዊና የህዝቦች መብቶች ኮሚሽን፣ በአፍሪካ *በነፃነት የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ መብት በአፍሪካ መመሪያ፣ 60ኛ መደበኛ ጉባዔ፣ ኒያሚ-ኒዤር፣ እ.ኢ.አ. 8-22 ግንቦት 2017፣ አንቀጽ* 13 http://www.achpr.org/files/instruments/freedom-associationassembly/guidelines_on_freedom_of_association_and_assembly_in_ africa_eng.pdf (በመጨረሻ የታየው እ.ኢ.አ. 30 ጥቅምት 2018)

[13] የአፍሪካ የሰብዓዊና የህዝቦች መብቶች ኮሚሽን፣ *በአፍሪካ በነፃነት የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ መብት በአፍሪካ መመሪያ፣ 60ኛ መደበኛ ጉባዔ፣ ኒያሚ-ኒዤር፣ እ.ኢ.አ. 8-22 ግንቦት 2017፣ አንቀጽ* 16 http://www.achpr.org/files/instruments/freedom-associationassembly/guidelines_on_freedom_of_association_and_assembly_in_ africa_eng.pdf (በመጨረሻ የታየው እ.ኢ.አ. 30 ጥቅምት 2018)

የሲቪል ማህበራት የመደራጀት መብት ላይ ዓላማና እንቅስቃሴዎቻቸው ላይ መጣል የሚችሉ ክልከላዎች በአለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 22(2) በጠባቡ ተገድበው ተቀምጠዋል፡፡[14]የመደራጀት መብት ላይ የሚጣል ማንኛውም ክልከላ በህግ የተደነገገ መሆን አለበት፡፡ በዚህ አንቀጽ በህግ መደንገጉ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ በዚህ በተጨማሪ ገደቡ ግለሰቦች እንቅስቃሴያቸው ከህጉ ጋር የሚጻረር ወይም የማይጻረር መሆኑንና የሚያስከትሉትን ህጋዊ ውጤት ለመገመት እንዲረዳቸው በቂ በሆነ መልኩ ግልፅ መሆን ይኖርበታል፡፡ በመቀጠል ገደቡ በአንቀጹ ውስጥ የተዘረዘሩትን አራት ቅቡል ዓላማዎች ለማሳካት የታለመ መሆን አለበት፡፡[15] እነዚህ ቅቡል ዓላማዎች በአንቀጹ ውስጥ የተዘረዘሩትን ብቻ የሚያጠቃልሉ ሲሆን ዓላማዎቹን በትርጉም ማስፋት የተከለከለ ነው፡፡ እነዚህ በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ቅቡል አላማዎች "በጠባቡ መቀረፅ ሲኖርባቸው እነዚህ አላማዎች ላይ ተመስርቶ የመደራጀት መብት ላይ መጣል የሚቻለው ገደብ አሳማኝና አስገዳጅ ምክንያት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡"[16]በሶስተኛ ደረጃ ገደቡ "ዲሞክራሲያዊ በሆነ ሕብረተሰብ ውስጥ አስፈላጊ የሆነ" መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህ የአስፈላጊነት መስፈርት መሰረት፣ የሚጣለው ገደብ ለማሳካት ከታሰበው ቅቡል አላማ አንጻር ተመጣጣኝ የሆነና አስፈላጊ ከሆነው መጠን በላይ መሆን የለበትም፡፡

የአፍሪካ የሰብዓዊና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽንም በመደራጀት መብት ላይ የሚጣሉ ሁሉም ገደቦች በአለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 22(2) የሰፈሩ መስፈርቶችን መከተል እንዳለባቸው ገልጿል፡፡[17] በተጨማሪ ኮሚሽኑ ያፀደቀው የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ ነፃነት በአፍሪካ መመሪያ "ሲቪል ማህበራት አላማና እንቅስቃሴያቸውን በነፃነት የመወሰን መብት አላቸው"[18] ሲል አስፍሯል፡፡

አምነስቲ ኢንተርናሽናል አንቀፅ 64(5) ላይ የተቀመጡት ግደባዎች በአለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 22(2) መሰረት መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች አያሟሉም ብሎ ያምናል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የውጭ በጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ ያነጣጠረ የ"አድቮካሲ እና ማሳመን" ስራዎች ላይ መሳተፍ አይችሉም የሚለው ገደብ እጅግ ሰፊ እና አሻሚ ስለሆነ በአለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 22(2) ስር የሚገኘውን የመደራጀት መብት ላይ በህግ የተደነገጉ ገደቦች በበቂ ሁኔታ ግልፅ መሆን አለበት የሚለውን መስፈርት አያሟላም፡፡ የአድቮካሲ እና የማሳመን እንቅስቃሴዎች በውስጣቸው ብዛት ያላቸው ተገቢና አስፈላጊ የሆኑ የውጭ በጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ሊያከናውኑዋቸው የሚችሉ ተግባራትን የሚያጠቃልሉ ሲሆን ስልጠና መስጠት፣ ጥናት እና ምርምር፣ የተለያዩ የህትመት ውጤቶችን እና የፖሊሲ ምርጫዎች ላይ ተፅዕኖ ሊኖራቸው የሚችሉ ህዝባዊ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀትን ያጠቃልላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ በጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የሰብዓዊ መብቶችን በተመለከተ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያላቸውን አቋምና ፕሮግራሞች ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ እንቅስቃሴዎችን የማድረግ ሙሉ ነፃነት በህግ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

---

[14] መንግስታት ገደቦችን ሲጥሉ ማሟላት ያሉባቸው መስፈርቶች አሉ፡፡ በመስፈርቶቹ ገደቡ በህግ የተደነገገ እና ዲሞክራሲያዊ በሆነ ማህበረሰብ ውስጥ ብሄራዊ ወይም የሕዝብ ደህንነትን፣ ሰላምና ፀጥታን፣ የህዝብ ጤና ወይም የሞራል ሁኔታን እና የሌሎችን መብቶችና ነፃነቶች ለመጠበቅ አስፈላጊ መሆን አለበት፡፡

[15] በአንቀጽ 22(2) ስር የሚገኘው የህጋዊ አላማዎች ዝርዝር፣ ማለትም ብሄራዊ ወይም የሕዝብ ደህንነትን፣ ሰላምና ፀጥታን፣ የህዝብ ጤና ወይም የሞራል ሁኔታን እና የሌሎችን መብቶችና ነፃነቶች፤ እንደማሳያ (illustrative) ሳይሆን ጠቅላይ (exhaustive) የሆነና በትርጉም መለጠጥ የማይችል ነው፡፡

[16] በተመሳሳይ የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ፍርድ ቤት የመደራጀት መብትን የሚያረጋግጠውን የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች የቃል ኪዳን ሰነድ አንቀጽ 11ን ሲተሮጉም እንዳለው "የመደራጀት መብት ላይ ገደብ ለመጣል አሳማኝና አስገዳጅ ምክነያቶች ብቻ ናቸው ተቀባይነት ያላቸው፡፡" *United Communist Party v. Turkey*, 4 Eur. Ct. H.R. 1 (1998) አንቀጽ 46፤ *Sidiroupoulos v. Greece*, 4 Eur. Ct. H.R. 500 (1998 Para 40); *Socialist Party and Others v. Turkey*, Application No. 21237/93 (1998), አንቀጽ 50ን ይመልከቱ፡፡. በተጨማሪ *Freedom and Democracy Party v. Turkey*, Application No. 23885/94 (1999); *Refah Partisi (The Welfare Party), Erbakan, Kazan, and Tekdal v. Turkey*, Application Nos. 41340/98, 41342/98, 41343/98, and 41344/98 (2001)ን ይመልከቱ፡፡ በተጨማሪ "የሲራኪውስ መርሆችን (Siracuse Principles) " ይመልከቱ [የተ.መ.ድ. ኢኮኖሞያው እና ማህበራዊ ጉዳዮች ምክር ቤት ስር መድሎን ለመከላከል እና በቁጥር አናሳ ዜጎችን ለመጠበቅ የተቋቋመው ንዑስ ኮሚቴ፣ Siracusa Principles on the Limitation and Derogation of Provisions in the International Covenant on Civil and Political Rights, Annex, UN Doc E/CN.4/1984/4 (1984)]፡፡ የሲራኪውስ መርሆች እ.ኢ.አ. በ1984 ዓ.ም. የአለም አቀፍ የህግ ባለሙያዎች ኮሚሽን፣ የአለም አቀፍ የወንጀል ህግ ማህበር፣ የአሜሪካን የአለም አቀፍ የህግ ባለሙያዎች ኮሚሽን፣ የአርባን ሞርጋን የሰብዓዊ መብቶች ኢንስቲቱት እና የወንጀል ሳይንስ ከፍተኛ ምርምር እንስቲቱት በጋራ ባሰባሰቡዋቸው የአለም አቀፍ ህግ ባለሙያዎች ፀደቀ፡፡ በህግ ገዢ ባይሆኖም መርሆቹ የአለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ውስጥ የተጠቃለሉ መብቶች ላይ እና የሀገራዊ የአስቸኳይ ጊዜ ሲታወጅ የሰብዓው መብቶች ላይ መጣል ስለሚቻሉ ገደቦችን በተመለከተ እንደ አሳማኝ የህግ ምንጭ ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ የሲራኪውስ መርሆችን ይህንን ሊንክ በመጫን ማግኘት ይችላሉ http://graduateinstitute.ch/faculty/clapham/hrdoc/docs/siracusa.html .

[17] የአፍሪካ የሰብዓዊና የህዝቦች መብቶች ኮሚሽን፣ *በአፍሪካ በነፃነት የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ መብት በአፍሪካ መመሪያ፣ 60ኛ መደበኛ ጉባዔ፣ ኒያሚ-ኒዤር፣ እ.ኢ.አ. 8-22 ግንቦት 2017፣* አንቀጽ 24 http://www.achpr.org/files/instruments/freedom-associationassembly/guidelines_on_freedom_of_association_and_assembly_in_ africa_eng.pdf (በመጨረሻ የታየው እ.ኢ.አ. 30 ጥቅምት 2018)

[18] የአፍሪካ የሰብዓዊና የህዝቦች መብቶች ኮሚሽን፣ *በአፍሪካ በነፃነት የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ መብት በአፍሪካ መመሪያ፣ 60ኛ መደበኛ ጉባዔ፣ ኒያሚ-ኒዤር፣ እ.ኢ.አ. 8-22 ግንቦት 2017፣* አንቀጽ 23 http://www.achpr.org/files/instruments/freedom-associationassembly/guidelines_on_freedom_of_association_and_assembly_in_ africa_eng.pdf (በመጨረሻ የታየው እ.ኢ.አ. 30 ጥቅምት 2018)

እንደዚህ ያለ የውጭ በጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ከአድቮካሲ እና ማሳመን ስራዎች የሚያግድ ሰፊና ጠቅላይ ድንጋጌ የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ስራ የሚያሰናክል እንዲሁም የመንግስት አካላት ገደቡን አለአግባብ እንዲጠቀሙበት መንገድ የሚከፍት ነው፡፡

በተጨማሪ ገደቡ በአለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 22(2) ቅቡል የገደብ አላማዎች/ምክንያቶች፤ ማለትም ብሄራዊ ወይም የሕዝብ ደህንነትን፣ ሰላምና ፀጥታን፣ የህዝብ ጤና ወይም የሞራል ሁኔታን እና የሌሎችን መብቶችና ነፃነቶች ለመጠበቅ ከሚሉት መካከል የትኛውን አላማ ለማስጠበቅ ተብሎ እንደተጣለ ግልፅ አይደለም፡፡ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ከእነዚህ አላማዎች ውጪ ሌሎች አላማዎችን በትርጓሜ በማጠቃለል የገደብ ምክንያት ማድረግ አይቻልም፡፡ እንዲሁም እነዚህ በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ህጋዊ አላማዎች "በጠባቡ መቀረፅ ሲኖርባቸው እነዚህ አላማዎች ላይ ተመስርቶ የመደራጀት መብት ላይ መጣል የሚቻለው ገደብ አሳማኝና አስገዳጅ ምክንያት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡ በአምነስቲ ኢንተርናሽናል እምነት የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ከአድቮካሲ እና ማሳመን ስራዎች የሚያግደው ገደብ የትኛውን ህጋዊ አላማ ለማሳካት ታስቦ እንደወጣ ግልፅነት መጉደሉ አሁን በስራ ላይ ባለው የበጎአድራጎት እና ማህበራት አዋጅ የሚንጸባረቀው  የውጭ በጎአድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን አለማመንና በጥርጣሬ የመመልከት አዝማሚያ እንዳልተቀረፈ ማሳያ ነው፡፡

ገደቡ በአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ህግ መሰረት ሊያሳካው የሚጥረው ተገቢ የሆነ አላማ አለው ተብሎ መከራከሪያ ቢነሳ እንኳን ገደቡ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ህግ የሚያስቀምጠውን የአስፈላጊነት መስፈርት አያሟላም፡፡ እንደዚህ ያለ ሰፊ፣ ግልፅነት የሚጎድለውና ጠቅላይ የሆነ ገደብ በምንም መልኩ የአስፈላጊነት መስፈርት ያሟላል ተብሎ አሳማኝ ምክንያት ሊቀርብ አይችልም፡፡ የመንግስት ስጋት የውጭ በጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን በአድቮካሲ እና ማሳመን ስራዎች ሰበብ የዲሞክሪያሳዊ ስርዓቱ ላይ ያልተገባ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ የሚል ከሆነ ድርጅቶቹን በነዚህ ተግባራት ሙሉ በሙሉ ከማገድ የተሻሉ ሌሎች እርምጃዎችን በመውሰድ ስጋቱን መቅረፍ ይችላል፡፡ ለምሳሌ በሀገሪቱ የምርጫ ስርዓቱን በተመለከተ የወጡ ህጎችን አግባብነትና ህጋዊ ቅቡልነት ባለው መልኩ መተርጎምና ያለአድሎ በሁሉም ባለድርሻ አካላት ላይ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው ማድረግ ዲሞክሪያሳዊ ስርዓት ውጫዊ ከሆነ ህገ ወጥ ጣልቃ ገብነት ለመከላከል ሁነኛ መሳሪያ ነው፡፡

ስለሆነም አምነስቲ ኢንተርናሽናል በረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 64(5) በውጭ ድርጅቶች ላይ የሚጥለው እጅግ ሰፊ ገደብ አላስፈላጊበመሆኑ ድርጅቶቹ አላማና እንቅስቃሴያቸውን በነፃነት ለመወሰን በሚያስሽል መልኩ መሻሻል ይገባዋል ብሎ ያምናል፡፡ አሁን ባለው መልኩ ከፀደቀ የውጭ በጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመተባበር ሊሰሩዋቸው የሚችሉ የተለያዩ እንደ ስልጠና፣ አቅም ግንባታ እና የመሳሰሉ ስራዎች አድቮካሲ እና ማሳመን ውስጥ ሊወድቁ ስለሚችሉ እንዳያከናውኗቸው ይገድባቸዋል፡፡ በተጨማሪ ሃገራዊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ክርክሮችን በተለይ ከሀር እድገት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸውን የአለም አቀፍ ንግድ፣ የመንግስት በጀት እና የአለም አቀፍ ብድርና እርዳታ በተመለከተ መደረግ የሚገባቸውን ውይይት የሚገድብ ይሆናል፡፡ ከዚህ ባለፈ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሲቪል ማህበራት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶች እንዲረጋገጡ ከሁሉም ድርሻ አካላት ጋር ተባብረው የመስራት መብታቸው ሊረጋገጥላቸው ይገባል፡፡

**ምከረ ሃሳብ፤**

***ሀ. ረቂቅ አዋጁ ሁሉም በጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት እንቅስቃሴያቸውን በነፃነትና ያለማንም ጣልቃ ገብነት ለመወሰን እንዲችሉ እና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት መፍጠር እንዲችሉ በሚያደርግ መልኩ መሻሻል አለበት፡፡***

*መ. ክትትል/ምርመራ እና ንብረት ማገድ*

*የረቂቅ አዋጅ አንቀፅ 77፡ ምርመራ የማድረግ ስልጣን*

1. *ከመንግስት ተቋማት፣ ከእርዳታ ሰጪ ድርጅቶችና ከህዝቡ በሚደርሰው ጥቆማ መሰረት ኤጀንሲው ማንኛውም በጎአድራጎት ድርጅትና ማህበር ስራውን በህጉ መሰረት ኢያከናወነ ስለመሆኑ ምርመራ ማከናወን ይችላል ፡፡*
2. *ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም፣ ኤጀንሲው ምርመራውን ከመጀመሩ በፊት ምርመራውን ለማካሄድ በቂ ምክንያት መኖሩን መወሰን አለበት፡፡*
3. *ኤጀንሲው ምርመራውን በፍጥነትና የበጎአድራጎት ድርጅቱን የእለት ከእለት ስራ በማያውክ መልኩ ለማከናወን የሚያስችሉ አስፈላጊ የሆኑ ዕርምጃዎችን ሁሉ መውሰድ ይኖርበታል፡፡*
4. *የኤጀንሲው ዳይሮክተር ኤጀንሲው ምርመራውን በሚያከናውንበት ወቅት የበጎአድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን ንብረትና ገንዘብ ማገድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝየድርጅቱ ወይም የማህበሩ ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ እንዲታገድ ትዕዛዝ ማስተላለፍ ይችላሉ ፡፡*

5. *የኤጀንሲው ዳይሮክተር የበጎአድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን ንብረትና ገንዘብ ለማገድ ያስተላለፈውን ንብረት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡*

ይህ አንቀጽ የመንግስት አካላትን የበጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ስራ ውስጥ ገደብ የለሽና ህገወጥ የሆነ ጣልቃ ገብነትን ሊጋብዝ የሚችል እና በአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ህግ መሰረት የመደራጀት መብት ላይ ሊጣሉ የሚችሉ ገደቦችን መጠን ያለፈ መሆኑ አምነስቲ ኢንተርናሽናልን አሳስቦታል፡፡ አሁን ባለው መልኩ ከፀደቀ አዋጁ የኤጀንሲው ዳይሬክተር በምርመራ ጊዜ የበጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ንብረትና ገንዘብ የማገድ ስልጣን ይሰጣቸዋል፡፡ የንብረትና ገንዘብ እገዳ በጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ስራቸውን ለመስራት እጅግ አስፈላጊ ከሆኑ ግብዓቶች በማቆራረጥ እንቅስቃሴዎቻቸውን የሚገታ በመሆኑ ከተለምዶ አሰራር የሚያፈነግጥ እርምጃ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በመሆኑም በጣም በተወሰኑ አስፈላጊ በሆኑ ሁኔታዎች ብቻ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የሚከናወን መሆን አለበት፡፡ የአፍሪካ የሰብዓዊና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን ያፀደቀው የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ ነፃነት በአፍሪካ መመሪያ እንዲህ ያለው የቁጥጥር ስልጣን የመደራጀት መብትን ከጥሰት ለመከላከል "በጥንቃቄ መገደብ" እንዳለበት ምክረ ሃሳብ ሰጥቷል፡፡[19]

ረቂቅ አዋጁ ለኤጀንሲው "በቂ የሆነ ምክንያት" ሲያገኝ ፍተሻ ማድረግን ጨምሮ የመመርመር ስልጣን ይሰጠዋል፡፡ "በቂ የሆነ ምክንያት" የሚለው ሀረግ ግን በጣም ሰፊ የሆነና ለኤጀንሲው በዘፈቀደ በበጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ስራ ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ መንገድ የሚከፍት ነው፡፡ ኤጀንሲው የበጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ መረጃ መሰብሰቡ አስፈላጊ ቢሆንም ይህ ስልጣን የበጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ለግላዊነት (privacy) ካላቸው መብት ጋር መመዛዘን አለበት፡፡ እነዚህ መብቶች ላይ የሚጣሉ ገደቦች በጠባቡ የተቀመጡ፤ ቅቡል የሆነ አላማን ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑ፤ እና ከአላማው አንፃር ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው፡፡

ረቂቅ ህጉ ኤጀንሲው መቼና በምን ሁኔታ ምርመራ ማካሄድ እንደሚችል ግልፅ በሚያደርግ መልኩ መሻሻል ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ኤጀንሲው የሚያከናውናቸውን ማናቸውም ፍተሻዎች በፍርድ ቤቶች ፍቃድና ክትትል ብቻ መከናወን እንዳለበት በረቂቅ አዋጁ ውስጥ መካተት አለበት፡፡ የአፍሪካ የሰብዓዊና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን ያፀደቀው የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ ነፃነት በአፍሪካ መመሪያ ባስቀመጠው መሰረት "ሲቪልማህበራት ላይ ተቆጣጣሪ አካላት የሚያከናውኗቸው ፍተሻዎች መከናወን ያለባቸው በፍርድ ቤት ትእዛዝ ብቻ ሲሆን ፍቃዱ ፍተሻው ያስፈለገበትን ህጋዊና ተጨባጭ ምክንያት በግልጽ መዘርዘር ይኖርበታል፡፡"[20]

የተባበሩት መንግስታት ልዩ ራፖረተርም የሲቪል ማህበራት የግላዊነት መብት እንዳላቸው በሚከተለው መልኩ አስተጋብተዋል፡-

"የመንግስት አካላት የሲቪል ማህበራትን የግላዊነት መብት በአለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 17 ላይ በተቀመጠው መሰረት የማክበር ግዴታ አለባቸው፡፡"[21]

በመሆኑም አምነስቲ ኢንተርናሽናል ረቂቅ አዋጁ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ንብረትና ገንዘብ ለማገድ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊጠይቅ የሚችልባቸው ግልፅና የተገደቡ ምክንያቶችን (ለምሳሌ ሙስና ስለመፈፀሙ የሚያመላክት ማስረጃ ካለ) እና ይህ ውሳኔ በይግባይኝ ሊታይ የሚችል መሆኑን በሚያረጋግጥ መልኩ መሻሻል አለበት ብሎ ያምናል፡፡

**ምክረ ሃሳብ፤**

**ሀ. የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 77 ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ምርመራን ማካሄድ የሚችልበትን ግልፅና የተገደቡ ምክንያቶችን በሚያስቀምጥ መልኩ እና ፍተሻዎች በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰረት ብቻ መከናወን እንዳለባቸው ግልፅ በሚያደርግ መልኩ መሻሻል አለበት፤**

---

[19] የአፍሪካ የሰብዓዊና የህዝቦች መብቶች ኮሚሽን፣ *በአፍሪካ በነፃነት የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ መብት በአፍሪካ መመሪያ፣ 60ኛ መደበኛ ጉባዔ፣ ኒያሚ-ኒዤር፣ እ.ኢ.አ. 8-22 ግንቦት 2017፣ አንቀጽ* 33 http://www.achpr.org/files/instruments/freedom-associationassembly/guidelines_on_freedom_of_association_and_assembly_in_ africa_eng.pdf (በመጨረሻ የታየው እ.ኢ.አ. 30 ጥቅምት 2018)

[20] የአፍሪካ የሰብዓዊና የህዝቦች መብቶች ኮሚሽን፣ *በአፍሪካ በነፃነት የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ መብት በአፍሪካ መመሪያ፣ 60ኛ መደበኛ ጉባዔ፣ ኒያሚ-ኒዤር፣ እ.ኢ.አ. 8-22 ግንቦት 2017፣ አንቀጽ* 21 http://www.achpr.org/files/instruments/freedom-associationassembly/guidelines_on_freedom_of_association_and_assembly_in_ africa_eng.pdf (በመጨረሻ የታየው እ.ኢ.አ. 30 ጥቅምት 2018)

[21] ተ.መ.ድ፣ *የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ ነፃነት ልዩ ራፖርተር ሪፓርት፣ ማይኒያ ኪያይ፣* የሰብዓዊ መብት ምክር ቤት 20ኛ ስብስባ A/HRC/20/27, እ.ኢ.አ. 21 ግንቦት 2012, አንቀጽ 65፣ https://www.ohchr.org/Documents/HRBodies/HRCouncil/RegularSession/Session20/A-HRC-20-27_en.pdf (በመጨረሻ የታየው እ.ኢ.አ. 30 ጥቅምት 2018)

**ለ. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ንብረትና ገንዘብ ማገድ የሚቻለው በአዋጁ ላይ በተቀመጡ የተገደቡ ሁኔታዎች፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ብቻ መሆኑን ግልፅ በሚያደርግ መልኩ መሻሻል አለበት፤ እና**

**ሐ. ረቂቅ አዋጁ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ምርመራን ለማካሄድ የወሰነውን ውሳኔና የኤጀንሲው ዳይሬክተር የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ንብረትና ገንዘብ ለማገድ ያስተላለፈውን ትዕዛዝ ምርመራው እየተካሄደ ባለበት ጊዜ ለመቃወም የሚያስችሉ ስነ ስርዓቶችን ባካተተ መልኩ መሻሻል አለበት፡፡**

ሠ. የአስተዳደር ወጪዎች ላይ የተጣሉ ገደቦች

*የረቂቅ አዋጅ አንቀፅ 64፡ የበጎ አድረጎት ድርጅቶችና ማህበራት የሥራ ነፃነት*

*9.የህዝብንና የሶስተኛ ወገኖችን ፍላጎት ለማስጠበቅ የተቋቋሙ በጎ አድረጎት ድርጅቶችና ማህበራት የአስተዳደር ውጪ ከገቢያቸው 20% በላይ መብለጥ የለበትም፡፡ ኤጀንሲው ይህ ገደብ ተፈፃሚ የማይሆንባቻው ድርጅቶችና ማህበራትን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፡ ፡ ለዚህ አንቀጽ አላማ፣ "የአስተዳደር ወጪዎች" ማለት ለድርጅቱ ወይም ማህበሩ ስራ ቀጣይነት አስፈላጊ የሆነና ፕሮጀክቶችን ለማስፈፀም የሚውሉ ወጪዎችን አያጠቃልልም፡፡ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ዝርዝሩን በደንብ ይወሰወናል፡፡*

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ስራቸውን ለማከናወን የሚያስፈልጋቸውን የተለያዩ ግብዓቶችን የማፈላለግና የመጠቀም መብት ለስራ ክንውናቸውና ለሲቪል ማህበራት መጠናከር ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው፡፡ ረቂቅ አዋጁ አሁን በስራ ላይ ባለው አዋጅ ውስጥ ያለውን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከሃገር ውጪ ያሉ የገቢ ምንጮችን እንዳይጠቀሙ የጣለውን ገደብ ማንሳቱ በጎ እርምጃ ቢሆንም፤የአስተዳደር ወጪን ከበጎ አድረጎት ድርጅቶችና ማህበራት ገቢ ከ20% በላይ እንዳይሆን የጣለው ገደብ  የበጎ አድረጎት ድርጅቶችና ማህበራት ስራቸውን ለማከናወን የሚያስፈልዋቸውን የተለያዩ ግብዓቶች የማፈላለግና የመጠቀም መብት ከመጠን በላይ የሚገድብ ነው፡፡ በንፅፅር በስራ ለይ ያለው የበጎ አድረጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ  የአስተዳደር ወጪ ላይ የሚጥለው ገደብ 30% ነው፡፡ ይህ ገደብ የበጎ አድረጎት ድርጅቶችና ማህበራት የሚሰበስቡት ገንዘብ ተጠቃሚዋች ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ታስቦ የተጣለ ቢሆንም፤ "የአስተዳደር ወጪዎች" የሚለው ሐረግ ግልፅ የሆነ ትርጉም የሌለው ሲሆን ትርጓሜውም እንደየድርጅቱ የሚለያይ ነው፡፡ ይህ የትርጉም ግልፅ አልባነት በአለምአቀፍ የሰብአዊ መብት ህግ መሰረት የመደራጀት መብት ላይ የሚጣሉ ገደባዎች ግልፅ መሆን አለባቸው የሚለውን የህጋዊነት መርህ የሚፃረር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የበጎ አድረጎት ድርጅቶችና ማህበራትን በኤጀንሲውና በሌሎች የመንግስት አካላት ከገደቡ አላማ አንፃር ላልተመጣጠነና ለዘፈቀደ ጣልቃ ገብነት ሊያጋልጥ የሚችል ነው፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት በላይ ገደቡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን የፋይናንስ ነፃነት የሚገድብና በአለም አቀፍ ህግ ተቀባይነት ያገኙ መርሆችን የሚቃረን ነው፡፡ ለምሳሌ የአፍሪካ የሰብዓዊና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን ያፀደቀው የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ ነፃነት በአፍሪካ መመሪያ "ህጉ ሲቪል ማህበራት በነፃነትየገቢ ምንጮችን ትርፍ አልባ ለሆኑ አላማዎች የመፈለግ፣ የመቀበልና የመጠቀም መብት እንዳላቸው በግልፅ ማስቀመጥ አለበት"[22] በማለት ያስረዳል፡፡

ረቂቅ አዋጁ ላይ ካለው በተቃራኒ አምነስቲ ኢንተርናሽናል ረቂቅ አዋጁ የበጎ አድረጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የበጎ አድረጎት ድርጅቶችና ማህበራት የሚያገኙትን ገቢ ለተጠቃሚዋች የታሰቡ ፕሮግራሞች ላይ እንዲያውሉ የሚያበረታቱ ስትራቴጂዎችን በተለይ የምርጥ ተሞክሮ መስፈርቶችን እንዲቀርፅ ኃላፊነት እንዲጥልበት ይመክራል፡፡ ይህ ለምሳሌ የበጎ አድረጎት ድርጅቶችና ማህበራትን የገቢ አጠቃቀምን የሚያመላክት የደረጃ መስጫ ስርዓት በመዘርጋት ሊያከናወን ይችላል፡፡

**ምከረ ሃሳብ፤**

**ሀ. በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 77 የሚገኘውን አስገዳጅ የከገቢ 20% የአስተዳደር ወጪ ጣረያ ተሰርዞ አስገዳጅ ባልሆነ የምርጥ ተሞክሮ ስታንዳርድ መተካት አለበት፡፡**

---

[22] የአፍሪካ የሰብዓዊና የህዝቦች መብቶች ኮሚሽን፣ *በአፍሪካ በነፃነት የመደራጀትና በሰላም የመሰብሰብ መብት በአፍሪካ መመሪያ፣ 60ኛ መደበኛ ጉባዔ፣ ኒያሚ-ኒዤር፣ እ.ኢ.አ. 8-22 ግንቦት 2017፣ አንቀጽ* 37 http://www.achpr.org/files/instruments/freedom-associationassembly/guidelines_on_freedom_of_association_and_assembly_in_ africa_eng.pdf (በመጨረሻ የታየው እ.ኢ.አ. 30 ጥቅምት 2018)